# የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
# Ethiopian Border Affairs Committee
**P. O. Box 9536 Columbus, Ohio 43209 USA E-mail: ethiopianborders@gmail.com**

ጥቅምት 23 ቀን 2004 ዓ. ም.
( November 3, 2011 )

ለፕሬዚዳንት ዑመር ሀሰን አህመድ አል-በሽር
የሱዳን ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት
ካርቱም፣ ሱዳን

ክቡር ሆይ!

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ( June 2, 2008 ) በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ያለውን የድንበር ሁኔታ አስመልክቶ ለክቡርነትዎ የጻፈውን ደብዳቤ ያስታውሳል። እርስዎም ይህን ዓቢይ ጉዳይ ላዘለው ደብዳቤ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተውታል ብለን እንገምታለን።

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል ያለው የድንበር ሁኔታ ለሁለቱም ወገኖች አሳሳቢ መሆኑን በመረዳቱ ጉዳዩን እንደገና ለእርስዎ ለማንሳት ተገዷል፤ የርስዎንም አፋጣኝ እርምጃ ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የጉዳዩን አሳሳቢነት በተደጋጋሚ ቢገልጽም ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ለችግሩ መፍትሔ መሻት ሲገባ፤ ኢትዮጵያና ሱዳን የድንበር ስምምነት መፈራረማቸውን በሚያሳዝን ሁኔታ ተከታትሎታል።

ይህ ዓይነቱ ስምምነት በሁለቱ አገሮች መካከል ለዘመናት ሊቆይ የሚችል ችግር ከማስከተሉ ባሻገር፤ በአካባቢው ሰላም፣ ደኅንነትና መረጋጋት ላይ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ ጠንቅ እንደሚኖረው ግልፅ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገሮች መካከል ያለውን ከፍተኛ መንግሥታዊ ምስጢሮችን ይፋ በማድረግ ልዩ ዝናን ያተረፈው ዊኪ-ሊክስ (Wiki Leaks) የተሰኘው ድረ-ገጽ በቅርቡ እንደገለጸው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሳያማክሩ በገዛ ችሮታቸው ከፍተኛ መጠን ያለውን የእርሻ መሬቶችን ለሱዳን መንግሥት እንደሰጡ በማያሻማ ሁኔታ ይፋ አድርጎታል። ይህንን ሕገ-ወጥ ተግባር የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ሙሉ በሙሉ አጥብቆ የሚቃወመዉ ከመሆኑም በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንኳንስ ይህን ያህል ሰፋፊ የእርሻ መሬት ቀርቶ አንዷት ስንዝር ቦታ እንኳን ለሱዳንም ሆነ ለሌላ መንግሥት የመስጠት ምንም ዓይነት ሕጋዊ መሠረት የላቸውም።

ቀደም ሲል በጻፍንልዎ ደብዳቤ አቶ መለስ ዜናዊ ከሱዳን መንግሥት ጋር የፈረሙትና የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልመከረበትና የይሁንታ ቃሉን ያልሰጠበት የመሬት ጉዳይ ተፈጻሚነት እንደማይሆንና ሕጋዊ ከለላም እንደሌላቸው ገልጸንልዎት ነበር።

አቶ መለስም ይህን ስምምነት እንደሚፈራረሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያውቅ ሊገጥማቸው የሚችለውን ከፍተኛ ተቃውሞ በመረዳታቸው ነው ስምምነቱን በምስጢር እንዲካሄድ ያደረጉት። ሌላው ቀርቶ ድርና ማጉ በኢሕአዴግ መርሕና አምሳያ የተዋቀረው ፓርላማ ተብዬው እንኳን በዚህ አንገብጋቢ ጉዳይ ላይ ውይይት ሳያደርግበት ነው ስምምነት መደረጉን የሰማው።

ከሁሉም እጅግ የሚያስደንቀው ነገር ጉዳዩን የዓለም ኅብረተሰብ በይፋ እያወቀው እያለ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ "አንድም ኢትዮጵያዊ ከይዞታው የተፈናቀለ የለም" እያሉ በተደጋጋሚ የሰጡት ከእውነት የራቀ የማስተባበያ ቃል ነው።

ለአያሌ ተከታታይ ትውልድ ሲያርሱበት ከነበረው የእርሻ መሬታቸው በኃይል የተፈናቀሉት ኢትዮጵያውያን በተፈጸመባቸው ግፍና በደል በዋናነት ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ተጠያቂ እንደሆኑ ቢታወቅም፣ በዚህ ረገድ የሱዳንም መንግሥት በሕዝባችን ላይ ለደረሰው ችግርና ለወደመው ንብረት ከተጠያቂነት የሚድን አይሆንም። ይህ ዓይነቱ አፍራሽ ተግባርም ከሁለቱ ሕዝቦች የረጅም ጊዜ የጋራ ጥቅም አኳያ ሲታይ ጠቀሜታ እንደሌለው እናምናለን።

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ ወደፊትም አቶ መለስ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያናጋ ማናቸውንም ዓይነት ውልና ስምምነት ቢደራደሩ ወይም ቢፈራረሙ፤ ኮሚቴው ተቃውሞውን ከማሰማትና ሁኔታውን ከማጋለጥ ለአፍታም ቢሆን ወደ ኋላ አይልም።

ክቡርነትዎ እንደሚያውቁት የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች ተቻችሎ አብሮ መኖር በሚለው መርሕ በመመራት ፍቅርና መልካም ጉርብትናን መሥርተው ለዘመናት አብረው የኖሩ ሕዝቦች ናቸው። እኛም እስከምናውቀው ድረስ ኢትዮጵያም ሆነች ሱዳን አንዱ በሌላው ላይ መሠረታዊ የሆነ የመሬት የይገባኛል ወይም የድንበር ጥያቄ አንስተው አያውቁም። በመሆኑም ሁለቱ ሕዝቦች በመሠረቱት በዚሁ የወንድማማችነት ስሜትና መልካም ጉርብትና የተነሳ ለሁለቱም ወገኖች የሚጠቅም የኢኮኖሚ ትስስር ዘርግተው በጋራ ተጠቃሚ በመሆን ይኸው እስከ ዛሬ በሰላም ይኖራሉ።

ለወደፊቱም ቢሆን በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ይህን የመሰለ መልካም ጉርብትና ቀጣይነት እንዲኖረው ከተፈለገ የሱዳን መንግሥት የበኩሉን ገንቢ አስተዋጽዖ የማበርከት ኃላፊነት አለበት።

በአንጻሩ ግን የሱዳን መንግሥት ከመልካም ጉርብትና ይልቅ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን የሚጻረር እርምጃ ከመረጠ ግን ከፍተኛ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል በግልፅ ሊታወቅ ይገባል። ችግሩ በሁለቱ አገሮች መካከል አለመረጋጋትና አስፈላጊ ያልሆኑ ግጭቶች እንዲቀሰቀሱ በማድረግ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፤ ለአካባቢውም ሰላም መደፍረስ ዓቢይ መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ክቡርነትዎ በሁለቱ አገሮች እስከዛሬ የቆየው መልካም ጉርብትና እንዲቀጥልና ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ከፍተኛ ግምት ይሰጣሉ ብለን እናምናለን።

በዚህ ረገድ ሱዳን እ.አ.አ. በ1964 ዓ.ም. በግብፅ ዋና ከተማ በካይሮ የአፍሪካ አህጉር መሪዎች የተፈራረሙት የአባል አገሮች የወሰን ክልል ነፃነታቸውን ሲያገኙ የነበረው ይዞታቸው እንዲከበር የሚደነግገውን ቻርተር ሱዳን ፈራሚ እንደመሆኗ መጠን፣ አሁንም የሱዳን መንግሥት ይህንን አህጉር አቀፍ ስምምነት ያከብራል ብለን እንገምታለን።

በእኛ እይታ ይህ የአፍሪካ መሪዎች ራእይ በአፍሪካ አገሮች መካከል ሊኖር የሚችለውን ማቆሚያ የሌለውን የርስ በርስ የድንበር ግጭቶችን አስቀርቷል ብለን እናምናለን።

በመሆኑም የሱዳን መንግሥት ይህን ክቡር አህጉራዊ መርሕ እንዲያከብርና ተግባራዊ እንዲያደርገው የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል።

ከዚህ በተጨማሪ ኮሚቴው በኢትዮጵያ ሕዝብና በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ወደ 2 ሚሊዮን በሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ስም የሱዳን መንግሥት ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ድንበርን አስመልክቶ ያደረገውን ስምምነት ተግባራዊ ከማድረግ እንዲታቀብ ጥሪውን ያስተላልፋል።የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው አገር-ከሃዲው የአቶ መለስ አስተዳደር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በመጻረር የሚያደርጋቸውን ማናችውንም ዓይነት ምስጢራዊ ስምምነትም ሆነ ውል ፈጽሞ አይቀበለውም። ምንም ዓይነት የድንበር ክለላም ሆነ ለውጥ ማድረግና በዚህም ረገድ ውል መፈጸም የሚቻለው በኢትዮጵያ ሕዝብ የተመረጠ መንግሥትና የሕዝቡ ይሁንታ ሲታከልበት ብቻ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አስተዳደር ለሱዳንም ሆነ ለሌላ ማናቸውም መንግሥት የኢትዮጵያን የግዛት አካል ቆርሶ ለመስጠት እንኳንስ ውክልና ቀርቶ ሕጋዊ ጠለላም እንደሌለው በድጋሜ ልንገልጽልዎ እንወዳለን።

በዚህ ረገድ ክቡርነትዎ ለዚህ ደብዳቤና በውስጡም ለሰፈረው አንገብጋቢ ጉዳይ ከፍተኛ አትኩሮት ይሰጡታል ብለን እንገምታለን።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር፤

1. የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
2. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት ( ኢዴኃሕ )
3. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ-ዴሞክራሲያዊ )
4. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ ( ኢዴኅአን )
5. የኢትዮጵያ መድህን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ( መድህን )
6. የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር ( ጋሕአዴግ )
7. የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ( ኢሕአግ )
8. የኢትዮጵያ ሀገራዊ ጉባዔ ( ኢሀጉ )
9. በስደት የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
10. የኢትዮጵያ አበይት ጉዳዮች መወያያ ሂደት
11. ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ( አኢጋን )
12. ጋሻ ለኢትዮጵያውያን

13. የኢትዮጵያ አየር ኃይል ማህበር
14. ተንሳዔ ንቅናቄ
15. እርምጃ ለነፃነት ( ማርች ፎር ፍሪደም)
16. ዓለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ሲቪክ ተግባር ንቅናቄ ( በቃ! )
17. ማኅደረ አንድነት የኢትዮጵያ ማህበር
18. የአኝዋክ ፍትህ ምክር ቤት
19. ለነፃነት ወደ ኢትዮጵያ
20. የዜጎች ቃል-ኪዳን
21. ደጀን ለዴሞክራሲ
22. እስከመቸ
23. የኢትዮጵያ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት መድረክ
24. የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር
25. ዓለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት
26. የኢትዮጵያ ምሑራን መረብ- ስካንዴንቪያ ቻፕተር
27. የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ-ካናዳ ( ኢፖእአኮ-ካናዳ )
28. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ድምጽ

ግልባጭ፥

Secretary of State Hillary R. Clinton
US Department of State
2201 C Street NW
Washington, DC 20520

Rep. John Boehner
Speaker of the US House of Representatives
H-232 the Capitol
Washington, DC 20515

Senator Harry Reid
US Senate Majority Leader
522 Hart Senate Office Bldg
Washington, DC 20510

H.E. Mr. Ban Ki-moon
United Nations Secretary General
1st Avenue, 46 Street
New York, NY 10017

President of the Security Council
United Nations
1st Avenue, 46 Street
New York, NY 10017

President, General Assembly
Of the United Nations
1st Avenue, 46 Street
New York, NY 10017

Embassy of the African Union
1875 I Street NW Suite 572
Washington, DC 20006

Delegation of the European Union
2300 M Street NW,
Washington, DC 20037

The League of Arab States
1100 17th Street NW Suite 602
Washington, DC 20006

Embassy of the Arab Republic of Egypt
3521 International Court NW
Washington, DC 20008

Embassy of the Republic of South Sudan
1233 20th Street, NW Suite 602
Washington, DC 20036

Embassy of Ethiopia
3506 International Dr. NW
Washington, DC 20008

Embassy of Kenya
2249 R Street, N.W.
Washington, DC 20008

Embassy of the Republic of Uganda
5911 16th Street, NW,
Washington, DC 20011

Embassy of the United republic of Tanzania
2139 R Street, NW
Washington, DC 20008

Embassy of the Republic of Rwanda
1741 New Hampshire Ave., NW
Washington, DC 20009

Embassy of the Republic of Burundi
2233 Wisconsin Ave., NW Suite # 212
Washington, DC 20007

The Embassy of the Republic of Zambia
2419 Massachusetts Avenue, NW
Washington, DC 20008

Embassy of the Republic of Mozambique
1525 New Hampshire Avenue, NW,
Washington, DC 20036

Embassy of South Africa
3051 Massachusetts Avenue, NW
Washington, DC 20008

Embassy of the Federal Republic of Nigeria
3519 International Court, NW
Washington, DC 20008

Embassy of Ghana
3512 International Dr. N.W
Washington, DC 20008

Embassy of the United Kingdom
3100 Massachusetts Avenue NW
Washington, DC 20008

Embassy of the Russian Federation
2660 Wisconsin Avenue NW
Washington, DC 20007

Embassy of the People's Republic of China
2300 Connecticut Avenue NW
Washington, DC 20008

Embassy of France
4101 Reservoir Rd. NW
Washington, DC 20007

Embassy of the Federal
Republic of Germany
4645 Reservoir Rd., NW
Washington, DC 20007

Embassy of Sweden
2900 K Street, NW
Washington, DC 20005

Royal Norwegian Embassy
2720 34th Street, NW
Washington, DC 20008

Embassy of Japan
2520 Massachusetts Avenue NW
Washington, DC 20008

Embassy of Canada
501 Pennsylvania Ave. NW
Washington, DC, 20001

Embassy of Mexico
1911 Pennsylvanian Ave. NW
Washington, DC 20006

Embassy of Brazil
3006 Massachusetts Ave. NW
Washington, DC 20008

Embassy the Republic of India
2536 Massachusetts Ave. NW
Washington, DC 20008

Embassy of the Republic of Israel
3514 International Dr. NW
Washington, DC 20008

Mr. Robert B. Zoellick
President of the World Bank
1818 H Street, NW
Washington, DC 20433

Mrs. Christine Lagarde
Managing Director
The International Monetary Fund
1900 Pennsylvania Avenue, NW
Washington, DC 20006

The United Nations High Commissioner for Refugees (UNHCR)
1775 K Street, NW Suite 300
Washington, DC 20006

Dr. Gregory Stanton
President of Genocide Watch
P. O. Box 809
Washington, DC 20044